# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 40 ቁ. 3 ታኅሣሥ 2007 ዓ.ም


## ታኅሣሥና ሰማዕታቱ ሲዘከሩ !

ከቅርቡ የሀገራችን ታሪክ ስንነሳ፤ ታኅሣሥና ሰማዕታት የተቆራኙ አንፀባራቂ ከዋክብት እንደሆኑ እንገነዘባለን። ከዋክብት ሰማዕታቱም የጀግንነት አሻራቸውን አሳርፈው ሄደዋል ። ይህም፣ ኢትዮጵያውያን ኩራታችንን የበለጠ ያጎለዋል። ተተኪው ትውልድም፤ አዳዲስ ሰማዕታት ማፍራቱን ይቀጥላል። የታኅሣሥ ጀግና ትውልድ የሚከበረው፤ በአይበገሬነቱና ቆራጥነቱ ብቻ ሳይሆን፤ እንከን በማይገኝለት ሀገር ወዳድነቱና በሕዝብ አፍቃሪነቱም ጭምር ነው። ይህንንም፤ በለገሰው ክቡር ደሙና በከሰከሰው ዕፁብ - ድንቅ አፅሙ አስመስክሮ ያለፈ በመሆኑ ነው። ከመሥዋዕት የተረፈው ኃይልም ፤ ያልደረቀ ደሙን እያከበረ፤ በማይቀረው መሥዋዕትነት ትግሉን ይቀጥላል። በመሆኑም ፤ የታኅሣሡ ዓላማና ራዕይ ግቡን መምታቱ አይቀርም።

ከአምሳዎቹ መጀመሪያ አንስቶ እስከ ስድሳ ስድስቱ አብዮታዊ ማዕበልና እስከ አሁንም ድረስ፤ በተካሄደው የለውጥ ፈላጊዎች ትግል፤ አያሌ ኢትዮጵያውያን በግንባር ቀደም መሥዋዕት ከፍለዋል። የ1953ቱ የመኮንንኖች የለውጥ እንቅስቃሴ፤ በወርሃ ታኅሣሥ እንደነበረ መጥቀሱም አግባብነት አለው። ከዚያ ታኅሣሥ ጀምሮ በተከታታይ፤ ለዴሞክራሲ ለውጥ ሲባል፤ ተማሪዎች፤ ወጣት ምሁራንና ሀገር-ወዳድ ዜጎች የህይወት ዋጋ ከፍለዋል። ሁሉም የታኅሣሥ ጀግና ሰማዕታት ናቸው። በዚህ ያላሰለሰ ትግል፤ ሕዝቡን በማንቃትና የዘውድ ሥርዓቱን ምንነት በማጋለጥ፤ ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ትግል ተካሂዷል። ያ ትውልድ፤ በለውጥ ፋና-ዊጊነት፤ ጉልኅ ሚና ተጫውቷል። ምን ጊዜም በአርአያነት የሚጠቀስ ጀግና ትውልድ ሆኖ አልፏል !

በተለይም፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሪ የነበረው ጥላሁን ግዛው፤ በዐፄው የደህንነት ኃይል ከተገደለ በኋላ፤ ተፈፍሞ በቀጠለው እንቅስቃሴ፤ በዩኒቨርሲቲው ቅፅር ግቢ በርካታ ተማሪዎች በግፍ ተረሸነዋል። በዚህ ምክንያት፤ ወረሃ ታኅሣሥ ፤ ዝከረ-ሰማዕታት እንዲሆን ተወስኗል። ከዚያ ጀምሮ ፤ ታኅሣሥን፤ በየዓመቱ ፤ የኢትዮጵያ ተማሪዎች የሰማዕታት ወር አድርገው ሲያከብሩት ቆይተዋል። እነኛ ተማሪዎች፣ በዘርና በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በጎሳ ሳይከፋፈሉ፤ የብሔር ዕኩልነት ለሚከበርባት፤ ለአንድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ነበር የተሰውት። ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ማስቀደም ነበር ዓላማቸው። ኢትዮጵያ ወይም ሞት እያሉ ነበር የተሰውት። ለሰማዕታቱ፤ ኢትዮጵያ ሀገራቸውና ዜጎቿ፤ ቀዳማዊም ደኃራዊም ነበሩ። ዐልፋና ዖሜጋቸው እነርሱ ብቻ ነበሩ። የዚያ ትውልድ አባላት፣ እነኛ ሰማዕታት፣ አንዳቸውም በጎሳና በነገድ በሽታ አልተለከፉም። ሲያልፍም አልነካቸው ነበር!

የታኅሣሣውያኑ መሥዋዕት ግን ከንቱ ሆኖ አልቀረም። የየካቲቱ ዐብዮት ተከስቶ፤ ሥር -ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ዐብይ ምክንያት ሆኖ ነበር። ሰማዕታትን እያከበሩና እየዘከሩ ለተተኪው ትውልድ የጀግንነትና የመሥዋዕትነትን ታሪክ ማስተላለፍ፤ የዜግነት ኃላፊነትና ተልዕኳችን እንደሆነ ይሰማናል፡፡ የሰማዕታቱ መንፈስ፣ የጀግንነት፣ የሀገርና የሕዝብ ፍቅር መንፈስ ነው። ይህ መንፈስ በጊዜና ቦታ የማይለወጥ ዘለዓለማዊ መንፈስ ነው። ከትውልድ- ትውልድ የሚተላለፍ ሀገራዊ ቅርስ ነው። ኢትዮጵያዊ ቅርስ! ይህ ቅርስ ሊመነጭ የሚችለው ደግሞ፤ ጥልቀት ካለው ሀገራዊ ስሜት እንጅ በጎሳዊ ጠባብነት ከተመረዘ ዘረኝነት አይደለም።

ኢትዮጵያዊነት ስሜትን ለመመረዝ የውጭና የውስጥ ጠላቶች፣ ሀገርንና ሕዝብን ለማዳከም በረዥሙ አቅደው የሚጠቀሙበት ስልት አንዱ በመሆኑ፤ የሥነልቦና ዘመቻ በሰፊው ያካሂዳሉ። ይህ ዘመቻ አሁንም በተጠናከር መልኩ ቀጥሏል። ተስፋ የቆረጠና ለራስ ጥቅም ብቻ የሚቆም እንጅ፤ ለሀገርና ለሕዝብ የሚሰዋ ትውልድ እንዳይፈጠር ይመኛሉ። አንድ የሆነ ሕዝባዊና ሀገራዊ ራዕይን አንግቦ እንዳይታገል ውዥንብር ይፈጥራሉ። በከፊልም ቢሆን፤ ይህ ስልት አልያዘላቸውም ማለት አይቻልም። የሩቅ ዓላማቸው፣ ሁለት ነው። አንደኛው የኢትዮጵያን ኀልውና ማክሰም ሲሆን ፤ ያ ካልተሳካላቸው ደግሞ፤ ሀገራችን፤ የተከፋፈለችና የተዳከመች ሀገር ሆና እንድትቀር ማድረግ ነው። ዛሬ፣ ይህን ተልዕኮ የሚፈጽም፤ በዘር ተደራጅቶ የመጣ ቡድን የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ተቀምጧል።

ከቅርብ ታሪካችን እንኳን ብንነሳ፤ የዐጼ ኃይለ ሥላሴ ዘውዳዊ ሥርዓት፤ ዘውዱን ይጋፋሉ ብሎ በጠረጠራቸው ስመ-ጥር ዐርበኞችና የመብትን ጥያቄ ባነሱ ምሁራን ላይ ከግድያ እስከ ግዞትና መሰደድ ያካተተውን አሰቃቂ እርምጃ በመውሰድ ፤ ብዙ ግፍና በደል ፈጽሟል። በአንፃሩ ግን፣ በጣሊያን ወረራ

ጊዜ፤ ሀገርን በመከዳት ወራሪውን ኃይል ሲያገለግሉ የቆዩትን ባንዳዎች፤ ሲሾምና ሲሸልም ኖሯል። ከዚህም በላይ የንጉሡን ሽሽት (ስደት) ያልተቀበሉ ለሀገርና ለነጻነት የተዋደቁትን ዐርበኞች አግልሏል። በላይ ዘለቀንና ደጃ. ታከለ ወ/ሐዋርያትን ገድሏል። ታዲያ ዛሬ የባንዳ ልጆች፤ በምኒልክ ግቢ ቢሸሹ ምን አዲስ ነገር ይሆናል?

የፋሽስታዊው የደርግ አገዛዝም ቢሆን፤ በኢትዮጵያ ስም እየማለ- እየተገዘተ፤ ለጥቂት የሥልጣን ጥመኛ መኮንኖች ሲባል፤ በታሪካችን ከፍተኛ መጥፎ ጠባሳ ጥሎ ሄዷል። በሕዝቡና በወጣቱ ትውልድ ላይ ያተኮረው ሽብር፤ ውጤቱ እስካሁን ድረስ፤ ሀገራችን ለገባችበት ወድቀት ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል። ይህ የታሪክ ጠባሳ፤ ለዴሞክራሲና ለፍትኅ-ርትዕ መከበር ሲባል የሚደረገው ትግል፤ እጅግ አስፈሪና አደገኛ ስለሆነ ማንም መታገል የለበትም የሚል ፍርሃት እንዲሰፍን አድርጓል። ለፖለቲካ ነጻነት መታገል፤ ጠንቁ ለቤተሰብም ይተርፋል ከሚል ድምዳሜ እንዲደርስ ምክንያት ሆኗል። "ፖለቲካና የኤሌክትሪክ ገመድ በሩቁ" "ኀመን በጤና" ...፤ በሚል ድባብ እንዲሸበበ እየተደረገ ነው። መታገል ካስፈለገም፤ **እየተገዙ መታገል ይሻላል** የሚል አሳፋሪ ባኅል እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ይገኛል። ይህ ሁኔታ፣ የታኅሣሳውያንን መንፈስና ዓላማ የሚጻረር ብቻ ሳይሆን ታሪካቸውንም የሚያኅድፍ ይሆናል። አጽማቸው ይህንን መስማት የሚችል ቢሆን ኖሮ፤ ከመቃብሩ ውስጥ ሆኖ ይገለባበጥ ነበር። ምክንያቱም፣ እየተዋረዱ መገዛት ኢትዮጵያዊነት አይደለምና !

ሀገረ-አናብስት ትባል የነበረችው ኢትዮጵያ፤ ዛሬ በየክልሉ የሚሸሎከለኩ ጃርቶች መፈልፈያ ሆናለች። ያስራ ሰባቱ ዓመታት የደርግ አገዛዝና የወያኔው የ24 ዓመታት የከፋፍለህ ግዛ ዘመን፤ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያሳደረው ከባድ ጉዳት በቀላሉ የሚጠገን ባለመሆኑ፤ የታኅሣሡን ጀግኖች ዓላማ ይዞ የሚታገለው ትውልድ በጽኑዕ ሊታገለው ይገባል። ሊያከሽፈውም ይገባል። ያን ካላደረግ፤ የሰማዕታቱ አፅም ይፋረደዋል። ተተኪው ትውልድም ይረግመዋል። ይንቀዋልም።

አሁን በደረስንበት የታሪክ ወቅት፤ ሕዝቡን እርስ በእርስ የሚያጫርስ፤ የዘርና የጎሳ መርዝ ሆን ተብሎ ከሚረጭበት አደገኛ ሁኔታ ላይ እንገኛለን። በታሪክና በሃይማኖት የነበሩትን የጋራ ዕሴቶቻችንን በማዛባትና በማደናገር፤ ለጋራ ዓላማና ለጋራ ሀገር በአንድነት ቆመን እንዳንታገል ከፍተኛ ውዥንብር እየነዛ ቢገኝም ውጤቱ ግን አልተሳካለትም። ይህ ስለተባለ ግን የወያኔን ተንኮል በአርምሞ መመልከት ማለት አይደለም። ይኽ ሥርዓት የሚነቀልበትን ሁሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አገዛዙ በሥልጣን ለመቆየት፤ ሕዝቡን እያናከሰና እየከፋፈለ መቀጠል ስላለበት ፤ ወጣቱን ከራሱ ብሔር ውጭ ስለሌላው ክልል እንዳያስብና እንዳያይ አድርጎታል። ሀገሩ ለባዕዳን ስትቸበቸብ፤ በአንዱ ክልል ሕዝብ ሲፈናቀልና ሲጨፈጨፍ፤ ሌላው ዝም ብሎ የሚያይበትና የማይቆረቆርበት ሁኔታ ይታያል። የእኔ ዘርና የእኔ ጎሳ

እስካልተነካ ድረስ፤ እኔን ስለሌላው ምን አገባኝ የሚል አመለካከት የሚንፀባርቅበት አዝማሚያ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ነው። ታኅሣሣውያን ይህንን ያነውሩታል። ይፀየፉታል። ያወግዙታልም።

በዘርና በሃይማኖት የተከፋፈለ ሕዝብ፤ ላንድ ሀገር፤ በአንድ ላይ ቆሞ የውጭና የውስጥ ጠላቶቹን ይመክታል ብሎ መገመት አይቻልም። ወያኔም ይህንን ተረድቶ፤ በዚህ ስሌት እየሰራ እንደሚገኝ በአለፉት 24 ዓመታት በግልፅ ታይቷል። ከዚህም አልፎ-ተርፎ፤ ለዘመናት፤ የባህላችንና የታሪካችን ቅርሳ-ቅርስ የሆኑት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ የነጻነትና የጀግንነት ድርሳናት፣ መዛግብትና ተቋማት- ገዳማት እየወደሙ ይገኛሉ። በምትካቸውም ያልነበሩና የሌሉ የፈጠራ ታሪኮች በመፈብረክ ላይ ናቸው። ይህም፤ ተከታዩ ትውልድ፤ መሪ ያጣና ታሪክ አልባ ሆኖ እንዲቀር የተዘጋጀ ሀገር-ገዳይ እርምጃ ነው። ዛሬ በወያኔ ከተዘጋጀው ሥርዓተ- ትምህርት፤ (ካሪኩለም) የሀገራችንን አኩሪ ታሪክና ተመስጋኝ ባህሎችን መዝግበው ያቆዩት ድርሳናት ተለቅመው ወጥተዋል። እየከሰሙ እንዲረሱ በመደረግ ላይ ናቸው። በኢትዮጵያ መጻሕፍት- ወመዘክር ተከማችተው የቆዩትን ታሪካዊና ድንቅ የሀገር ሀብቶች ፤ በሀራጅ እንዲሸጡ መደረጋቸው ህያው ምስክር ሆኗል። ይህ አሳፋሪ ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባር ነው። የታሪክ ምርምር ማዕከላትም በአገዛዙ የፖለቲካ ውሳኔ ተዘግተዋል። የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልትም ፈርሷል። በአንፃሩ ደግሞ የወያኔ ካድሬ ለነበረው ሰው፤ የድንጋይ ቅርፅ ቆሞለታል። ዛሬ ለወያኔ ካድሬ ድንጋይ ቢቆለል፤ ነገ መፍረሱ አይቀርም። የፈረሰው የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልትም፤ ነግ-ተነገ ወዲያ ወደ ታሪካዊ ቦታው በክብር ይመለሳል።

ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን በሚሉት ላይ የሚደረገው ቅስቀሳም፤ ለሀገር- ለሕዝብ በቆራጥነት መታገልና መሥዋዕትም መክፈል፤ ጊዜው ያለፈበት የፋራ (የሞኝ) ፖለቲካ ዘይቤ እንደሆነ በመሰበክ ላይ ይገኛል። በአንጻሩ ደግሞ፣ ጥርስ የለሽ- የተሰለበና የሰለለ ተለማማጭ ድምፅ ማሰማት፤ የሠለጠነ- የተራቀቀ የሆነ ትግል እንደሆነ ይነገራል። ይህንን ትጥቅ አስፈች ስብከት ከሚያራምዱት ውስጥ፤ በአለፉት ሦስት ሥርዓቶች፤ ካባቸውን እየለዋወጡ የቆዩ ሰዎች ይገኙበታል። መታፈር በከንፈር እንጅ በሸበት ብቻ እንዳልሆነ አልተገነዘቡትም። የዚህ ዓይነቱ ትግል ስልት አቀንቃኞች፣ ለወያኔ የልብ -ልብ ሰጥተውታል። አወቁትም አላወቁት ወያኔ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ረድተውታል። እርሱም ፤ የልብ ወዳጆቹ ስለሆኑለት ተንከባክቦ- አሽሞንሙኖ ይዟቸዋል። ቆራጦቹ ምሁራንማ በመስዋዕት ታሪክ ሰርተው አልፈዋል። የታኅሣሣውያንን መሥዋዕት ፅዋ ቀምሰው፤ ዓርዓያ ሆነው ሄደዋል! አኩሪ ታሪካቸው ግን በመሥዋዕትነት ተምሳሌነቱ፣ አንፀባራቂ ኮከብ ሆኖ ይኖራል - እስከ ወዲያኛው ደረስ ! እስከ ዳግም ምፅዐቱ !

የሠለጠነ ፖለቲካ ትግል እናራምዳለን የሚሉ ስብስቦችና ቡድኖች፤ መሪዎቻቸውን አሳስረው፣ አሰድደውና አስገድለው፣ የማይቆጡና የማይጮሁ ሆነዋል። ይባስ ብለውም፣ የወያኔ ምርጫ አጃቢዎች እየሆኑ

ቀርተዋል። በአጃቢነት ሚናቸው፤ የፖለቲካውን ድባብና የትግሉን ሜዳ አጣብበውታል። " **የገበያ ግርግር፤ ለሌባ ይመቸዋል**" እንዲሉ፤ ወያኔም፣ የሁኔታው ተጠቃሚ ሆኗል። ለአንድ የቀድሞ የጂዮግራፊ መምህር " **አዲዮ ጅዮግራፊ** " ተብሎ እንደተቀለደባቸው ሁሉ፤ የሠለጠነ ፖለቲካ እናራምዳለን የሚሉ ቡድኖችም፤ እንዲሁ ዛሬ " **አሮማይ ፖለቲካ** " ደህና ሁኚ ፖለቲካ ተብሎላቸዋል። በማንኛውም ሥርዓተ-ማኅበርም ሆነ፤ ሥርዓተ መንግሥት የሚኖር ኅብረተሰብ፤ ለሚኖርበት ወቅት በትክክል የሚገልጽና የሚስማማ ይትብሃል ይናገራል። አብሶማ፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የተለመደ ነው።

ወርሃ ታኅሣሥን ስንዘክር፤ ሰማዕታቱን በመሥዋዕትነታቸው ብቻ ሳይሆን፤ የሀገሪቱ ችግር እየተባባሰ ለመሄዱ እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል ጭምር እንደነበርም እንገነዘባለን። በዘውዳዊ አገዛዝ የነበረችው ሀገር፤ ችግሯ አስቸኳይ መፍተሄ ካላገኘ፤ ህልውናዋ ሳይቀር፤ አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል አስቅድመው ጮኸው ነበር። የለውጥ ማዕበል በኢትዮጵያ ፖለቲካ አድማስ ላይ እያንዣበበ መምጣቱ እንደማይቀር ተንብየውም ነበር። ሀገራቸውን ከልብ የሚወድዱ ታኅሣሣውያን፣ የሠላም ለውጥና የመንግሥት ሽግግር ተደርጎ፤ ሕዝብ የሚሳተፍበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መምጣት ወሳኝ መሆኑን በተለያየ መንገድ ገልጸዋል። ለዚህም ውድ የህይወት ዋጋ እስከ መክፈል ድረስ በቅተዋል። የዚያ ሥርዓት አራማጆች ግን፤ አክራሪ አቋም ስለነበራቸው፤ ምክንያታዊ አዕምሮ- አልባ ሆኑ። የካቲት 66 ሕዝባዊ አመፅ መጥቶ፤ ጎርፉ ወሰዳቸው። አፍነው ሲገዙት የነበረውን ሕዝብ፤ ለለውጥ ሳያዘጋጁት በመቅረታቸው፤ ለሰው- በላው ወታደራዊ አምባገነን አጋልጠውት ሄዱ። የታኅሣሣውያን ትዕንቢታዊ ማስጠንቀቂያም ደረሰ። ሥርዓቱ ከሥር-መሠረቱ ተፈነገለ። ሀገሪቱም አደጋ ላይ ወደቀች። መሰናዶ ያልተደረገለት ለውጥም፣ ሁነኛ ባለቤት በማጣቱ፤ ከየጦር ሰፈሩ ተጠራርተው በመጡ ግለሰቦች እጅ በመውደቁ፤ የታኅሣሣውያኑ ተስፋና ራዕይ ግቡን ሳይመታ ቀረ። ኢትዮጵያ ሀገራችንም ከአንድ ፅንፍ አክራሪ ፊውዳል ሥርዓት- ወደ ሌላ አዲስ ጽንፍ አክራሪ ወታደራዊ አምባገነን ተዘዋወረች። የታኅሣሥ ጀግኖች መንፈስም፤

“አስቅድመን ነቅተን ተንብይተን ነበረ፤
መሥዋዕትም ከፍለን አሳይተን ነበረ፤
የሚሰማን ጠፍቶ፤ የሀገራችን ዕድል፤ እንዲህ ሆኖ ቀረ !”

እያለ ይጮኻል ፤ ዛሬ !

የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ፣ ከአንድ አክራሪ ፅንፍ ወደ ሁለተኛና ሦስተኛ ጽንፍ እያከረሩ በሚለዋወጡ የፖለቲካ ነውጠኞች አገዛዝ እየወደቀች የምትሄድ ሀገር ሆና ቀረች። በመጨረሻም፣ የራሷ ህልውና፤ የዜጎቿ አንድነትና ነጻነት በሞትና በሽረት መከከል እንዲሆን ተደረገ።

ይህ ሁኔታ፤ የታኅሣሣውያን ሰማዕታት ዓላማና ምኞት አልነበረም። አክራሪነትና ፅንፈኝነት፣ እንኳንስ በፖሊቲካ ዘይቤና ሂደት ቀርቶ፣ በቤተሰብና በጓደኝነትም ቢሆን አጥፊና -ጠፊ ከመሆን አያድንም። በተለይማ የጠብመንጃን ቃታ ተንተርሶ የሚመሠረት አክራሪነት፤ በማን ይነካኛል ትዕቢት ላይ የተመሠረተን ፍራቻንና ጥላቻን ይዞ ስለሚመጣ፣ ሀገርን አጥፍቶ ራሱንም አጥፍቶ እንደሚጠፋ የቅርብ ታሪካችን ህያው ምስክር ሆኗል።

የወያኔ አገዛዝ አራማጆች፣ በባኅርያቸው ፅንፈኞች፤ በዘረኛነት ፖለቲካቸው ደግሞ አክራሪዎች ናቸው። የፅንፈኝነት ባኅርያቸው የመነጨው፣ ከፍርሀትና ከጥላቻ በመሆኑ ድርጊታቸው ልክ እንደ ቆሰለ አውሬ ነው። ከፍርሀትና ከጥላቻ የሚመነጭ ጭካኔ ምን እንደነበር፤ ከደርግ አገዛዝ መማር በተገባ ነበር - አስተዋይ ኅሊና ያለው ቢገኝ ኖሮ ! የወያኔ ሰዎች፣ የሚፈሩትንና የሚጠረጥሩትን ሁሉ ይነክሳሉ። እያደሙ ያጠፋሉ። ዓላማቸው፣ የሆነውን ሁሉ እያደረጉ በሥልጣን የሚቆዩበትን ዘዴ ሁሉ ማመቻቸት ነው። ከዚህ ብዥታ በመነሳት ከአንድ ከንቱ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። የልብ ልብ እንዳገኙም ይቆጥሩታል። የሚጠላቸው ሁሉ የሚፈራቸው፣ የሚሸሻቸውና የሚሽቆጠቆጥላቸው ይመስላቸዋል። ባለጌን ሲያከብሩት፤ ሁሉም የሚፈሩት ይመስለዋል። **" ሆዱ ጠግቦ የተኛው ሁሉ ብስና ያገሳል እንጅ፤ ህልም አያይም "** እንደሚባለው፤ የወያኔ አገዛዝ አራማጆችም በጥላቻና በፍራቻ ድባብ ውስጥ ስለሚኖሩ፤ በብሩኅ ተስፋ ላይ የተመሠረተ ራዕይ ኖሯቸው ለሀገር- ለወገን የሚጠቅም ሥራ ያከናውናሉ ተብለው አይጠበቁም። ከአክራሪነትና ከፅንፈኝነት ሊላቀቁ አይችሉም። ለሀገራዊ ዕርቅና ሠላም ሊያስቡ አይቻላቸውም።

ያለፈው የዕርስ -በዕርስ ውጊያ ያስከተለው ደም መፋሰስ አልበቃ ብሎ፤ ዛሬም ለሌላ ዙር ጥፋት ሕዝቡን እያዘጋጁትና እየገፋፉት ይገኛሉ። " **በሰይፍ የኖሩ በሰይፍ ይጠፋሉ**" እንደተባለው፤ በመጨረሻ በሰይፍ የሚጠፋው ማን እንደሚሆን ታሪክ ምስክርነቱን ወደፊት ያረጋግጣል። ሕዝቡም፣ ያን የታሪክ ምስክርነት ለመስማት፣ ለማየት ጓጉቶ ይጠብቃል። ይህ ወቅት ደግሞ ሩቅ አይሆንም።

በአሁኑ ወቅት ሕዝባዊ አመፅ በየደረጃው እየተቀጣጠለ ይገኛል። በአልገዛም ባይነቱ በግንባር ቀደም የሚታወቀው የጎጃምና የጎንደር ሕዝብ አሻፈረኝ ብሎ ተነስቷል። በደብረ ማርቆስ፣ በባህርዳር፣ ባርማጭኾ፣ በጸገዴ፣ በሙሴባምብ ያለው ነዋሪ፤ የትግል ጥሪውን በማሰማት ላይ ነው። የድረሱልን- ተባበሩልን ጩኸቱን ካስመዘገበ ቆይቷል። በሌሎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚኖረው ሕዝብ ካልተነሳና ተባብሮ ካልቆመ፣ የወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ታጣቂ ጦር፤ አምጾ የተነሳውን ሕዝብ በየተራ ይጨፈጭፈዋል። አዝመራውንና ከብቱንም ያወድመዋል። ወንድ ሴት፣ ህጻን -ሽማግሌ፣ ህሙማን- ድኩማን ሳይለይ ሁሉንም ያጠፋል። ይህ አሰቃቂ ድርጊት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ነገር አይደለም።

በጣልያን ወረራ ዘመን፣ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ (ካሚሻ {ቻ} ኔራ) በሚል ስያሜ በሚታወቀው የሙሶሊኒ ነፍሰ ገዳይ ጦር፣ የአረመኔ ተግባር እንደፈጸመ፣ ታሪክ መዝግቦታል። በዘመነ ደርግም፤ ነበልባል የተሰኘ ፈጥኖ- ደራሽ ጦር የፈጸመውን አሰቃቂ ድርጊት ስናስታውስ ይዘገንነናል ። ዛሬ፣ ወያኔም በአቅሙ በናዚ ጀርመን ጌስታፖ አምሳያ በተደራጀው ነፍሰ-ገዳይ፣ የወያኔ ፌዴራል ጦር አማካኝነት በአመፅ ላይ ያለውን ሕዝብ ያለ ርህራሄ እንደሚጨፈጭፍ ሁሉም ሊገነዘበው ያስፍልጋል። ሕዝባዊው አመፅ በመላው ሀገሪቱ ካልተቀጣጠለ በስተቀር፣ በመንጠባጠብ የሚደረግው እንቅስቃሴ የታሰበውን ግብ ሊመታ አይችልም። ያመረቃ ግብ ማስመዝገብ የሚቻለው ደግሞ፤ ሕዝባዊ አመፅ በተጠናከረና በውል በተደራጀ ማዕከላዊ ዕዝ ተቀነባብሮ ሲመራ ብቻ ነው።

ማንኛውም ሰው ራሱን ለማታለል ካልፈቀደ በስተቀር፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ የሕዝቡን አመፅ አስተባብሮ የሚመራ ማዕከላዊ ዕዝ ( ሴንትራል ኮማንድ ) የለም። ይህ እንዲፈጠር የተደረገው ሙከራ ሁሉ እስካሁን አልሰራም። ይህ እንዳይሆን የተደረገው፣ ፍላጎቱና ምኞቱ ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን፤ ቁርጠኝነቱና ለመሥዋዕት ዝግጁነቱ በመጥፋቱ ነው። ወያኔን ከሥልጣን ለማውረድ፤ የአብዛኛው ተቃዋሚ አመለካከት፤ ሁለት ልብ ነው - **ሁለት ባላ በመያዝ ፤ አንዱ ሲሰበር በሌላው ተንጠልጠል** የትግል ስልት አይሰራም። በአንድ ዓላማ ጸንቶ፤ ለአንድ ዓላማ ግብ መምታት ቆርጠው ካልታገሉ፤ እስካፍንጫው የታጠቅን አምባገነን አገዛዝ፣ መገልበጥ ቀርቶ ማስደንገጥ አይቻልም። የተባበረ ሕዝባዊ አመፅ፣ ከመቅፅበት አምባገነን ገዥዎችን ከሥልጣናቸው እንዴት እንዳስወገዳቸው፤ በሰሜን አፍሪካ የተከናወነው **"የዐረብ ፀደይ"** በሚል ቅፅል የሚታወቀው የዐረብ ሕዝቦች አመፅ ታሪክ ፤ የቅርብ ትምህርት ሊሆን ይገባል።

"አንድነት ኃይል ነው! " የሚለው መርኅ፣ ለርዕስ አንቀጽ መጻፊያና ለሠላማዊ ሰልፍ ማስተጋቢያ ብቻ ሳይወሰን፤ በተባበረ ኃይል ከተመራ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግቡን እንደሚመታ ማንም የሚጠራጠር የለም። ዐባይ ኢትዮጵያን ለማዳን፤ ዐብይ ሆኖ መታገል አማራጭ አይኖረውም።

በግማሽ ምዕተ ዓመት የትግል ሂደት በሀገራችን ብዙ ታጎሣሦች እየመጡ ሄደዋል። በርካታ ሰማዕታትም ታሪክ እየሠሩ አልፈዋል። ኢትዮጵያ ሀገራችንም የወላድ መካን ባለመሆኗ አሁንም ትግሉን ሳያቋርጡ የሚያካሂዱ ልጆች አላጣችም። ዛሬ ትግሉን በጽናት የቀጠለው ኃይል፤ ከታኅሣሣውያኑ ሰማዕታት ጋር፤ በደምና አፅም፣ ዕትብት የተያያዘ ነው። በዓላማና በራዕይ፤ በመንፈስና በባኅርይ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ ቀጥሏል። የማይበገር ኢትዮጵያዊ ኃይል ሆኖ ይታገላል። ችንፈትና ፍርሃት፤ ልምምጥና ተስፋ መቁረጥ በእርሱ በመዝገብ- ቃላት ውስጥ አይገኙም። ይህ ፅኑ ባኅርይ የኢትዮጵያዊነት አንድያ መግለጫ ሆኖ አቆይቶታል።

የዚህ ሁሉ መሠረት ደግሞ መተኪያ ሊኖረው የማይችል ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያዊነት ሲባል መሬቱና አፈሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝቧንም ጭምር አብሮ ያከብራል ይወዳል። ፍቅሩንም፣ በመሥዋዕትነት ይገልፃል። እኛ፣ በገዥዎቿ የተበደለችውን ሀገርና ተጎሳቁለው የሚማቅቁትን ዜጎቿን ስናስብ፤ የኢትዮጵያዊነት መግለጫችን እንደሆነ እንቆጥረዋለን። ኢትዮጵያዊ ዜግነት ዕሴቱ፣ በዜግነት ምክንያት ለሚገኝ የኢኮኖሚ ጥቅማጥቅምና ትርፋትርፍ ሳይሆን፤ የታሪኩን፣ የባኅሉን፣ የዕምነቱን፣ የነፃነቱንና የሕዝቡን ክብርና ፀጋ የሚያጠቃልል እንደሆነ እንረዳለን። ኢትዮጵያ ስንል የመከራዋና የደስታዋ ተካፋዮች፤ የማግኘቷና የማጣቷ ተሳታፊዎች እንጅ እንደ ወያኔ፤ " ለእኛ ያልሆነች ሀገር፤ ትበጣጠስ " የሚባልባትን ኢትዮጵያ ማለታችን አይደለም። ዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ በዘለዓለማዊ ሰማዕታት ጀግኖቿ መሥዋዕትነት እስካሁን ቆይታለች። ወደፊትም ትኖራለች በሚል ፅኑ ዕምነት ከመታገል ሌላ ምርጫ እንደሌለ ተገንዝበን፤ በቀጣይነት መታገልን መርጠናል። ይህ ምርጫችን ምን ያህል የመንፈስ ደስታ እንደሚሰጥ፤ ታጋይ የነበረው ሁሉ ያውቃዋል። ሊያውቅ የማይፈልግ ደግሞ ሊያውቅ አይችልም።

በየዓመቱ የሚመጣው ወረሀ-ታኅሣሥ፤ ለኢትዮጵያ ሰማዕታት መዘከሪያና ታሪካቸውንም ማክበሪያ በመሆን በመላው ታጋይ ዘንድ በአክብሮት ተዘክሮ የሚውል ወር ነው። የሰማዕታቱ የጀግንነትና የቆረጥነት ታሪክ ይታወሳል። ይወደሳል። ይቀደሳል። ትግሉንም የቀጠለው ኃይል ፤ የትግሉን ቃል-ኪዳን የሚያድስበት ወር ነው። ለአዲሱና ለተተኪው ትውልድም ትምህርት ማስተላለፊያ መድረክ ነው። ተተኪ የሌላት ሀገር በመሆኗ፣ በዘለዓላማዊነቷ ፀንታ የምትኖር ኢትዮጵያ መሆኗ ባይካድም፤ ትውልዱ ግን እየተተካ መሄዱ፤ የታሪክ ሐቅና የተፈጥሮ ሕግ መሆኑ አያከረክርም። ለቋሚቷ ሀገር፣ ቋሚ የሆነ አኩሪ ታሪክ አስመዝግቦ ማለፍ፤ የቱን ያህል አኩሪ መሆኑን የታኅሣሥ ሰማዕታት በደማቸው ጽፈው አልፈዋል። በህልፈታቸውም ህያው መሆናቸውን አስመስክረዋል። በመስዋዕትነት ማለፍ ህያውነት እንጅ ኅልፈት እንዳልሆነም አስተምረው ነው ያለፉት።

መሥዋዕታዊ ኅልፈት፤ መሞት ሳይሆን ህይወት ስለሆነ፣ ለታህሣሥ ጀግና ትውልድ አፅም ፤ ዘለዓለማዊ ክብርና ምስጋና እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም ለዘለዓለም ትኖራለች !